# ፍቅር

*በግርማ ወ/ሩፋኤል*

«እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን ዐውቀናል እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።» ፩ዮሐ.፫፥፲፮

በዓለማችን ላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች ታላላቅ የኪነጥበብ ሰዎች የታወቁ ፈላስፎች ስለፍቅር ብዙ ብለዋል። ይሁን እንጂ የእውነተኛውን ፍቅር ምንነቱን የገለጹት፣ በተግባርም ያዋሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው። እውነተኛ ፍቅር ብዙ ስለተጻፈበት ወይም ተደጋግሞ ስለተነገረ ከሰው ልቦና አይገባም። እውነተኛ ፍቅር ከእግዚአብሔር የሚገኝ የተለየ ጸጋና የክርስትና ሃይማኖትም መሠረት ነው። «ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ።» የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ እርስበርሳችን እንዋደድ» ፩ዮሐ.፬፥፯፣ ሮሜ. ፭፥፭።

የሰው ልጆች በሃይማኖት ጸንተው በአገልግሎትም ተጠምደው ቢኖሩ ከዚያም አልፈው ንብረታቸውን ለነዳያን እየሰጡና እየመጸወቱ መላ ሕይወታቸውን ቢያሳልፉ ቢጾሙ ቢጸልዩ ቢሰግዱ የሕግጋት ማሠሪያ የሆነውን ፍቅርን ካልያዙ ከንቱ ነው። ፩.ቆሮ.፲፫፥፪-፫። ፍቅር ከሌለ ሰላም የለም። ፍቅር የሌለው ሰው ተስፋ ቢስ ነው። ራሱን ይጠላል። ቅናትና ምቀኝነትን ተመልቶ የሌሎችንም ሰላም ይነሣል። ኃጢአትን ያለ ይሉኝታና ያለገደብ ይፈጽማል። ሸንጋይና በመጨረሻም ሃይማኖት የለሽ ይሆናል። መዝ.፲፬ በአንጻሩ ፍቅር ካለ የጎደለው ይሞላል፤ የጠመመው ይቃናል፤ መራራው ይጣፍጣል፤ ጥቂቱም ይበዛል። «ፍቅር የኃጢአትን ብዛብ ይሸፍናልና» ፩ጴጥ.፬፥፰፣ ማቴ.፲፬፥፲፱-፳፣ ምሳ.፲፯፥፩።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለደቀመዛሙርቱ አደራውንና ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ «እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።» በማለት ፍቅርን ምሳሌ ሆኖ አስተምሯል። ዮሐ.፲፭፥፲፪። ለዚህ ነው ፍቅርን ሐዋርያት

የትምርታቸው መጀመሪያና ማሣረጊያ ያደረጉት፣ ሊቃውንትም በመጽሐፍታቸው ሰፊ ዓምድ የሰጡት፣ መዘምራን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የዘመሩት::

### ማንን ነው የምናፈቅረው?

ክርስቲያን እውነተኛ ፍቅር ሊኖረው ይገባል:: የሚያመልከው የፍቅርን አምላክ ነውና:: ይህም እውነተኛ ፍቅር ሁለት ዘርፎች አሉት::

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ:: ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት:: ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርስዋም:- ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት:: ኦሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ::» ማቴ.፳፪÷፴፯-፵::

### ፍቅረ እግዚአብሔር

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ:: ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት:: ማቴ.፳፪÷፴፯:: የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ባለውለታነቱን ዐውቆ ይወደው ያመለከው ያመሠግነው ክብሩንም ዘወትር ይናገር ዘንድ ያስፈልጋል:: ፍቅረ እግዚአብሔር እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆነውን ሁሉ በመውደድም ይገለጣል::

*ሀ. ትእዛዛቱን በመጠበቅ*

«... ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤» ዮሐ.፲፬÷፳፩::

«የሚወደኝ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ::» ብሎ በፍቅር የጠራን አምላክ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሎ ሕጉን በፍቅር አስቀመጠልን:: ማር.፰÷፴፬፣ ዮሐ.፲፬÷፲፭ ሥጋውን ቆርሶ ደሙንም አፍስሶ በሞቱ ፍቅርን አስተማረን:: ይህንን ፍጹም ፍቅሩን አስበን ስለምንወደው እንታዘዛለን:: ስለዚህ ለክርስቲያኖች የተሠጠን የሐዲስ ኪዳን ሕግ የፍቅር ሕግ ነው:: ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው፤» ያለው ሮሜ.፲፫÷፲:: በመሆኑም ፍቅረ እግዚአብሔር ፈቃዱን በመፈጸማችን ትዕዛዛቱን በመጠበቃችንና





ለእርሱም ከእውነት በመገዛታችን ይገለጻል:: «ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና:: ፩ዮሐ.፭÷፫::

*ለ. ቅዱሳኑን በመውደድ*

«... እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃን::» ፩ዮሐ.፭÷፪::

ፍቅረ ቅዱሳን ለምእመናንን ሁሉ የተሰጠ ታላቅ ጸጋ ነው:: በመሆኑም ኦርቶዶክሳውያን እግዚአብሔር ለወደዳቸውና ላከበራቸው ቅዱሳን የተለየ ፍቅር አለን:: ሮሜ.፰÷፴:: ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብለው ለጽድቅ የተሰደዱትን ነቢያት ቃሉን በዓለም ሁሉ ዞረው ያስተማሩትን ሐዋርያት በስሙ መከራ የተቀበሉትንና ደማቸውን ያፈሰሱትን ሰማዕታት በሕይወት ዘመናቸው በተጋድሎ የኖሩትን ጻድቃን አገልጋዮቹን መላእክት መውደድ እግዚአብሔርን መውደድ ነው:: ስለዚህም ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳንን እናከብራቸዋለን፣ ዘወትርም ስማቸውን እየጠራን በአማላጅነታቸው እንማጸናለን:: ይህም እውነተኛ ፍቅር ምድራውያንን ከሰማያውያን ጋር ያገናዝበናል:: በኋላም አንድ ያደርገናል:: ይህ ፍቅር ነው ጌታችን በቤተልሔም ሲወለድ ሰዎችንና ሰማያውያን መላእክትን አንድ ዓይነት ዝማሬ ያዘመራቸው፣ አንድ ዓይነትም ምሥጋና እንዲያቀርቡ ያደረጋቸው:: ሉቃ.፪÷፫::

*ሐ. የአገር ፍቅር*

አገራችን ኢትዮጵያን የምንወዳት ወንዝ ተራሮችዋ ልምላሜዋ የተለየ በመሆኑ አይደለም:: ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ሕገ ኦሪትን ቀድማ የተቀበለች በሕገ ወንጌልም የጸናች ታቦተ ጽዮንን እና ግማደ መስቀሉን ስለያዘች ቅዱሳን በኪደተ እግራቸው የባረኳት ለእመቤታችንም በአሥራትነት የተሰጠች የቃል ኪዳን ሀገር ስለሆነች ነው:: በመሆኑም የአገር ፍቅር ከፍቅረ እግዚአብሔርና ከቅዱሳን ፍቅር ጋር ይገናኛል:: አባቶቻችን ይህ ፍቅር ኖሯቸው ነው ነፃነቷንና አንድነቷን አስከብረው ያቆዩልን:: በሰላምና በነፃነት የሚኖሩበት አገር ከሌለ እግዚአብበሔርን በነፃነት ማምለክ ለእርሱም መገዛት አይቻ ልም:: በመሆኑም ክርስቲያን

አገሩን ሊያፈቅር ያስፈልጋል:: ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር ስለ አገር ፍቅር የምታስተምረው፣ ስለ አገር ሰላምም የምትጸልየው::

ኢትዮጵያውያን ይህ ፍቅር በልቦናቸው ስላለ በየትኛውም ዓለም ቢኀዙ ወገናቸውን የሚወዱ በራሳቸው ስም የሚጠሩ በራሰቸው ትውፊትና ሃይማኖት የሚመሩ ናቸው:: ዛሬ መናፍቃን የሚሯሯጡት በእውነት ወንጌልን ሊሰብኩን ሳይሆን ለዚህች የቅዱሳን ሀገር ለሆነች አገራችን ያለንን ፍቅር ለማጥፋት እና ግድየለሾች እንድንሆን ለማድረግ ነው:: ወንጌልን መስበክ እውነተኛ ዓላማቸው ቢሆንማ ኖሮ በአገራቸው ወንጀልን፣ ዝሙትን፣ የእፅ ሱሰኝነትን...መቆጣጠር ተስኗቸውና ስንቱስ ወገናቸው ወንጌል ጠምቶት አልነበር?!

## ፍቅረ ቢጽ

«... ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን፤» ፩ዮሐ.፬÷፳-፳፩::

ፍቅረ ቢጽ /ባልንጀራን መውደድ/ ማለት በሥላሴ አርአያ የተፈጠረን የሰውን ልጅ ሁሉ በሰውነቱ መውደድ ማለት ነው:: ክርስቲያን የሰውን ክፉ ምግባሩን ይጠላል እንጂ ሰውየውን ስለ ሰውነቱ አይጠላም:: በመሆኑም ክርስቲያን አብሮት ካለው ባልንጀራው ወይም ወንድሙ ጀምሮ ለነፍስ እስከሚፈልገው ጠላቱ ድረስ ሊወደው ይገባል:: ይህ ማለት ግን በሃይማኖት ከማይመስለንና የቤተ ክርስቲያን ጠላት ከሆነው ጋር እንተባበር፣ አንድ እንሁን ማለት አይደለም:: እንደዚህ ዓይነቱ ፍቅር ሳይሆን ሞኝነት ነው:: ይህንንም «በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት:: ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፣ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና» በማለት ሐዋርያው በሚገባ ገልጾልናል:: ፪ዮሐ.፲ ይህንን ባለመረዳትም ነው ብዙዎች በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ጋር አጉል ወዳጅነት ፈጥረው በመጨረሻ የካዱት፤ ከፍቅረ





እግዚአብሔርም የተለዩት:: በመሆኑም በፍቅረ ቢጽ ጠላትን እስከ መውደድ መድረስ ማለት ሃይማኖትን የሚያስክድ ከፍቅረ እግዚአብሔርም የሚለይ ይሁን ማለት አይደለም:: ፍቅረ ቢጽ የሚገለጠው በሃይማኖት ነውና! ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስም «ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም ቢሆን ኃይላትም ቢሆኑ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን እንዳይችል ተረድቼአለሁ፤» ያለው:: ሮሜ.፰÷፴፰-፴፱:: ስለዚህ በሃይማኖት ከማይመስሉን ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ጋር /በጋብቻ፣ በዝምድና፣ በጓደኝነት፣ ወዘተ .../ መወዳጀትና የጥፋታቸው ተባባሪ መሆን ፍቅረ ቢጽ ሊሆን አይችልም:: «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመጻ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ፪ቆሮ.፲፮÷፲፬»::

ይሁን እንጂ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰውም ሆነ በጊዜያዊ ግጭት የተጣሉት ሰው ቢኖር ከጥፋቱ ሳይተባበሩ ቢቸገር በመርዳት በቀል ሳይዙ በጸሎት በማሰብ ፍቅርን መግለጽ ያስፈልጋል:: «... ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው» ሮሜ.፲፪÷፳:: ይህንንም የሴፍ በጠላትነት ለሸጡት ወንድሞቹ ቅዱስ እስጢፋኖስም በድንጋይ ለወገሩት ወገኖቹ ይቅርታ በማድረግ ፈጽመውታል:: ዘፍ.፵፭÷፩-፲፭፣ የሐዋ.፯÷፷:: እነ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራም ጠላትን በጸሎት በማሰብ በግብር አውለውታል::

ዛሬ ብዙዎች ስለ ፍቅረ ቢጽ ሲናገሩ እንጂ በተግባር ሲያውሉት አይታይም:: ከቤተሰባቸው ጀምሮ ሰላም የላቸውም፣ አንዳቸው ሌላውን በክፋት ዓይን ያያሉ፤ ከጐረቤቶቻቸው ጋር ስምምነት የላቸውም፤ በሥራ ቦታ እርስ በርሳቸው ይቀናናሉ ይጨቃጨቃሉ ነገር ግን ስለ ፍቅር ይሰብካሉ:: ፍቅር አላቸው የሚባሉትም ፍቅራቸው የታይታና ውጭአዊ ነው:: አንዳንዶችም ወረተኞች ናቸው፤ ፍቅራቸው ጊዜአዊና የአንድ ሰሞን ብቻ ያውም በጥቅም ላይ የተመሠረተ:: ነገር ግን እውነተኛ ፍቅር በቃላት ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፤ ራስን ለሌላው አሳልፎ እስከ መስጠት የሚያደርስና በተግባር የሚገለጥ እንጂ! «... በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ፤» ፩ዮሐ.፫÷፲፰

## ፍቅረ ቢጽ በተግባር እንዴት ይገለጻል?

### ሀ/ በመርዳት

ፍቅረ ቢጽ የተራበን በማብላት የተጠማን በማጠጣት፣ የታረዘን በማልበስ፣ ያዘነን በማጽናናት፣ የታመመን በማከምና በማሳከም፣ ... ይገለጻል:: ይህ በፍኖተ ኢያሪኮ በዱላ ተቀጥቅጦ የወደቀውን መንገደኛ እንድናስታውስ ያደርገናል:: ይህ ሰው ቀና አድርጎ ውኃ የሚያጠጣው ቁስሉን የሚያክምለት እውነተኛ ወዳጅ ይሻ ነበር:: ብዙዎች ከንፈራቸውን መጠውለታል:: ፊሪሳውያንም እያዩ አልፈውታል:: ሣምራዊው ግን ደረሰለት፤ ተቀጥቅጦ የወደቀውንና የተሰቃየውን መንገደኛ አስነሥቶ ቁስሉን አከመለት:: የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጎ ፍቅሩን ገለጠለት:: እውነተኛ ወዳጁም ሆነ:: ሉቃ.፲፥፴፬-፴፯:: እውነተኛ ፍቅር እንደዚህ በተግባር የሚገለጥ እንጂ በመመቸትና ባለመመቸት፣ በማግኘትና በማጣት ተወስኖ በቃላት የሚቀር አይደለም::

እንዲሁም ክርስቲያን ቤተሰቡን ሊረዳ ላሳደጉት ወላጆቹ መልካም ነገር ሊያደርግ ያስፈልጋል:: ይህንን ሳይፈጽም ለተቸገሩት ሁሉ ሲመጸውት ቢውል ፍቅሩን ገልጧል ማለት አይቻልም:: «ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው፤» ፩ጢሞ.፭፥፰::

### ለ- በንዳጌ በቀልንት

ክርስቲያን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሰው ጋር ሊጋጭ ይችላል:: ይሁን እንጂ ቂም ሊይዝና ሊበቀል አይገባም:: «... በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁን መርቁ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ ስለ ሚያሳድዷችሁ ጸልዩ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና::» ማቴ.፭፥፵፬-፵፭:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጠላት መልካም ማድረግ እንደሚገባ ከገለጸ በኋላ «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» በማለት ጎደጌ በቀል መሆን እንደሚገባ ተናግሯል:: ሮሜ.፲፪፥፳፩:: ስለዚህ ፍቅረ ቢጽ በቀል ሳይዙ ለጠላት መልካም በማድረግና በጸሎት በማሰብ ሊገለጽ ይገባል::





### ሐ. በማስተማር

እውነተኛ ፍቅር ገንዘብን በማውጣት እንዲሁም በጉልበትና በዕውቀትም ይገለጣል:: ፍቅር ያላቸው ገንዘባቸውን በመስጠት የተቀሩትም በጉልበታቸው ሲረዱ መምህራንም ደግሞ ዕውቀታቸውን በማካፈል ይገልጡታል:: ኃጢአተኛውና እውነተኛው መንገድ የጠፋው ቃለ እግዚአብሔርን ሰምቶ በንስሐ እንዲመለስ ማይምነትና ድንቁርና እንዲጠፋ ማስተማር ፍቅረ ቢጽ ነው::

ከዚህም ሌላ «ፍቅር ይታገሳል ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም የራሱንም አይፈልግም አይበሳጭም በደልን አይቆጥርም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመጻ ደስ አይለውም፣ ሁለን ይታገሳል ሁሉን ያምናል ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይጸናል፤» ፩ቆሮ.፲፫፥፬-፯::

በአጠቃላይ እውነተኛ ፍቅር የሃይማኖት ዋልታ የምግባራት ራስ ነው:: ያለ ፍቅር ሃይማኖተኛ መሆን ለእግዚአብሔር መገዛትም አይቻልምና! ፍቅር የተለያዩትን የሚያዋሕድ የተራራቁትን የሚያቀራርብ የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሰላምን የሚያንጽ የሕይወት መሠረት ነው:: ሌላው ይቅርና አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው «ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት» ብሎ እንደተናገረው አምላካችንን ከሰማያዊው ዙፋን ያወረደው፣ እስከሞትም ያደረሰው ፍቅር ነው:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለሙን ወድዶታልና፤» ዮሐ.፫፥፲፮

እንግዲህ አምላካችንን እስከ ሞት ያደረሰውን ፍቅሩንና ለእኛ ያደረገልንን ውለታውን እያሰብን ለሕጉ በፍቅር ተገዝተን እርስበርሳችን» እየተዋደድን ለሰማያዊ መንግሥት እንድንበቃ የእርሱ የአምላካችን ፈቃድ የቅዱሳን አማላጅነት አይለየን::

## «ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው።» /ሰቆ.ኤር.፫÷፳፮/

*ቀሲስ ያሬድ ገ/መድኅን*

በመከራ ዘመን ለእስራኤል ልጆች የተነገረ ቃል ነው። ተናጋሪው ነቢዩ ኤርምያስ ነበር። ነቢዩ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ ውጭ በመሆናቸው ለመከራ የተጋለጡ በምርኮ ምክንያት በባዕድ ሀገር የሚሰቃዩ ወገኖቹን የፈጣሪን ምሕረት በዝምታ ጠብቁ ይላቸዋል። በራሳቸው ጥበብ ምርኮን እናስወግድ ብለው አላስፈላጊ ስሜትነት ውስጥ እንዳይገቡ ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር የሚሠራውን በዝምታ እንዲጠብቁ ይመክራቸዋል።

ዝምታ አስፈላጊ ነው። የፈጣሪያችሁን ምሕረት ተስፋ እያደረጋችሁ በዝምታ ጠብቁ የተባለውም ለዚህ ነው። በመሠረቱ «ዝምታ» ስንል ዓይነቱ ብዙ ነው። ለምሳሌ ሲናገሩን ሲተቹን ... ሰምቶ መልስ አለመስጠት ዝምታ ነው። መንፈሳዊ ሰው ሰምቶ ማሳለፍ ስላለበት ነቃፊዎች ቢመጡበት ተናግረው የሚያናግሩ ቢቀርቡት በዚህ የዝምታ ዓይነት /መልስ ባለመስጠት/ ድል ይነሳቸዋል። ጌታችን በስቅለቱ ወቅት አይሁድ ሲሰድቡት በዝምታ ሲሰማቸው የምናየው ለዚህ ነው። ይህ ዝምታ ግን ሁልጊዜ ላይሠራ ይችላል። አንዳንዴ አስፈላጊ የማይሆንበት ጊዜ አለ። ሃይማኖትን የሚደፍር፣ በሕልውና ላይ የሚነጣ ትህትናን እንደ ስንፍና የሚቆጥር ሲኖር በመጠኑም ቢሆን መናገር ያስፈልጋል። ነቢዩ ኢሳይያስ «ስለ ጽዮን ዝም አልልም» ይለናል። ኢሳ.፷፪÷፩። የእናታችን የጽዮንን ክብር የሚያቃልሉትን በዝምታ ማሳለፍ አልችልም። ክብሯን እየመሰከርኩ መልስ እሰጣቸ ዋለሁ ሲል ነው። አባ እንጦንስ በዘመኑ ከበዓቱ ወጥቶ አያውቅም። መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ላይ ሲነሡ ግን ሃይማኖትን ለመመስከር መናፍቃንን ለማሳፈር ይወጣ ነበር። ምክንያቱም ወቅቱ በዝምታ የሚታለፍ ስላል ነበረ ነው። ከዚህ ውጭ በራስ ህልውና ላይ ሲመጡ መብትን ሲነጠቁም መናገር የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። አባ አጋቶን ድንጋይ ጎርሶ





የኖረ አባት ነው። ድንጋይ ከጎረሰ በኋላ ተናግሮ አያውቅም። ሰይጣንም ብዙ ጊዜ እየመጣ ይሰድበው እርሱም ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ያሳልፍ ነበር። አንድ ቀን ግን «መናፍቅ አንተ» ብሎ ስለሰደበው ይህን ሰምቶ ማሳለፍ አልቻለም። ስለዚህ ድንጋዩን አንሥቶ «መናፍቅ»ንን አይደለሁም ብሎ መለሰ። ሆኖም መብት ሳይጣስ ሃይማኖታዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ሳይሆን በተገኘው ሁሉ ግን መናገር አይገባም።

የሰው ልጅ በድርጊቱ የሚናገርበት ወይም ዝም የሚልበት ወቅት አለ። ለምሳሌ አንድ ሰው ፈጣሪው ሁሉን እንደሚያደርግለት አስቦ አንተ ታውቃለህ በማለት ለፈጣሪው ሁሉን ቢሰጥ ይህ ዝምታ ነው። ማድረግ የሚገባውን አድርጎ ከዚህ በላይ የአንተ ፈንታ አይደለም፣ ያሰብኩትን አስፈጽመኝ ብሎ ውጤቱን ለአምላኩ ቢተው ይህ ዝምታ ነው። በተቃራኒው ደግሞ ያሰብኩት ካልተሳካ ብሎ ቢጨነቅ ሐሳብ ቢያበዛ ከዝምታ ውጭ መሆኑ ነው። የድርጊት ዝምታ የሚባለው መታ ገሥ ልቅደም አለማለት ነው።

ከላይ ባየነው ምዕራፍ የተጠቀሰውም ይህ ነው። ሰው ዝም ብሎ እግዚአብሔርን ተስፋ ያድርግ ያለው በትዕግሥት ሆኖ መንገዱን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥቶ ሳይጨነቅ ሐሳብ ሳያበዛ በተስፋ ይጠብቅ ሲል ነው።

ነቢዩ እንዳለው የሰው ልጅ ሲቸገር ሲጎሳቆል ሲራብ ሲጠማ ራሱን ሁሉን ማድረግ ለሚችል ፈጣሪ ሰጥቶ መታገሥ አለበት። አለበለዚያ ግን የፈጣሪውን ቸርነት ተስፋ ማድረግ ትቶ በራሱ ጥበብ ለመጓዝ ቢሞክር ሕይወት በራሱ ውስብስብ ይሆንበታል። ነገሮች ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነው ይበላሹበታል። ጌታችን «ከእናንተ ተጨንቆ ከቁመቱ ላይ አንድ ክንድ የሚጨምር ማን ነው» /ማቴ.፮÷፳፯/ እንዳለ ሰው በገዛ አካሉ ላይ የሚሆነውን እንኳን መቆጣጠር የማይችልበት ወቅት አለ። ስለዚህ ሁል ጊዜ ራሱንም ሆነ በዙሪያው ያለውን ለፈጣሪው መስጠትና መታገሥ ይገባዋል።

አንዳንድ ጊዜ ውስጣችን ሰላም ሲያጣ ያሰብነው አልሳካ ሲለን የእግዚአብሔርን ቸርነት እንረሳለን። ትላንት አብሮን የነበረውን ዛሬም

አብሮን ያለውን ነገም ረጅሙን ጉዞ የሚያስጉዘንን አምላክ እንዘነጋለን:: በራሳችን ጥበብ የምናመጣው ያለ ይመስል ችግሮችን ለመፍታት ብቻችንን ተነሥተን ያለ የሌለ ኃይላችንን እንጠቀማለን:: እግዚአብሔርን ትተን በራሳችን እንሮጣለን:: ግን ሁሉም እንዳሰብነው አይሆንም:: እርሱ በወሰነው ሰዓትና ወቅት ካልሆነ በእኛ ሐሳብ የሚሆን ስለሌለ የሩጫችን ፍጻሜ በተነሣንበት ቦታ መልሰን ማረፍ ይሆናል:: ስለዚህ የሰው ልጅ ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን እየጠበቀ በተስፋ ቢጽናና በትዕግሥት መጨረሻውን ቢመለከት መልካም ነው::

አባታችን አዳም ከገነት ሲወጣ ያጣትን ርስት ለማግኘት ብዙ እንደጣረ መጻሕፍት ይነግሩናል:: ደሙን ከእህል ጋር ለውሶ እስከ ማቅረብ ደርሶ ነበር:: ግን ይህንን ሁሉ ቢያደርግም ገነትን ማግኘት አልቻለም:: እርሱ ባሰበው ወቅትና ጊዜ ወደ ቦታው አልተመለሰም:: በዚህ ፈንታ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተገባለት:: ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ተባለ:: ይህንን የተስፋ ቃል የሰማው አዳም አልተከራከረም:: አንተ ፭ሺ፭፻ ዘመን ብትልም እስከዚያው እኔ በራሴ እሞክራለሁ በሦስተኛውና አራተኛው ሺህም ልገባ እችላለሁ አላለም:: ከዚህ ይልቅ ሲያል ሆኖ የተገባለት ቃል ኪዳን እስኪፈጸም መጠባበቅ ጀመረ:: በእርሱ ሩጫና ጥበብ የሚያመጣው ስለሌለ የአምላኩን ቸርነት እየጠበቀ ቆየ:: እግዚአብሔር ትዕግሥቱን አይቶ ደረሰለት:: በወሰነለት ጊዜና ሰዓት ከሞት አዳነው::

በእኛም ሕይወት ያጣነውን የምናገኝበት ያሰብነው የሚሳካበት ጊዜ አለ:: ለዚህ ግን በትዕግሥት መጠበቅ ይገባናል:: አዳምን ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ያዳነ ፈጣሪ እንደማይረሳን አስበን መታገሥ ይኖርብናል:: ዝምታ የተባለው ይህ ነው:: አንተ ሁሉን ማድረግ ትችላለህ ብሎ ለፈጣሪ መስጠት፤ የአምላክን መለኮታዊ ጥበብ በትዕግሥት መጠበቅ::

አረጋዊው ስምዖን የጌታችንን መወለድ ሳያይ እንደማይሞት ተነገረው:: ሉ.ቃ.፪÷፳፭:: ጊዜው ደርሶ የፈጣሪውን ልደት እስኪመለከት





፫፻ ዘመን ኖረ:: እርጅና እየተጫነው ሰውነቱ እየደከመ ቢሄድም ሁሉን በትዕግሥት ጠበቀ:: እግዚአብሔር የገባለት ቃል ኪዳን ነበርና ይኸው እስኪፈጸም ቆየ:: እኔም እርጅና ተጫነኝ አንተም ዘገየህ አላለም:: አንተ የምትቆይ ከሆነ እኔን ውሰደኝ ብሎ አለመነም:: ሁሉን በጊዜው የሚፈጽም አምላክ በጊዜው እንደሚያሳየው አምኖ ጸና:: በዚህ የተነሣ በእርጅናው ወራት ከቤተ መቅደስ ሲወጣ የተሰጠው ቃል ኪዳን ተፈጸመለት:: ጌታችንን በእናቱ እቅፍ ሆኖ አየ:: ከዚህ በኋላ ነው «ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋል፤ እንግዲህ እንደ ቃልህ ባሪያህን ታሰናብተዋለህ» ያለው:: /ሉ.ቃ.፪÷፳፱/::

ዓይኖቻችን የእግዚአብሔርን ማዳን የሚያዩበት በሰላም ግቡ የምንባልበት ጊዜ አለ:: የጎበጠ ሲቀና የተበላሸ ሲስተካከል የጠፉ ሲመለስ... የምናይበት ጊዜ አለ:: ቢዘገይም እግዚአብሔር ሊሠራው ያሰበው ሁሉ አንድ ቀን ይከናወናል:: የቤተሰባችን የራሳችንና የቤተ ክርስቲያን ችግርና ጭንቀት ተወግዶ የምናይበት ጊዜ ይኖራል:: ይህን ወቅት መቼም ይሁን መች የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እኛ እንደስምዖን ዓይኖቻችን ማዳኑን የሚያዩበት ጊዜ በትዕግሥት /በዝምታ/ መጠበቅ ነው ድርሻችን::

አባታችን አብርሃም ዘሩ እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚበዛ ተነገረው:: /ዘፍ.፲፭÷፭/:: ይህን ቃል ከሰማ በኋላ ግን ተፈተነ:: ልጅ ሳይወልድ ለብዙ ዘመን ኖረ:: እርሱም ሚስቱም እስኪያረጁ ድረስ ፍሬ አልባ ሆነው ቆዩ:: እንዲያውም ሣራ ልጅ መውለድ አትችልም የሚባልበት የእርጅና ደረጃ ደረሰች:: በሴቶች ያለ ልማድ ከሰውነቷ ቀረ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ለምን ብለው አልተቃወሙም:: በመጨረሻ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት:: ሚስቱ ሣራ ፀንሳ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ፣ ማኅፀኗን አለምልሞ ዘር እንደሚሰጣት ነገረው::

የእኛም ሕይወት እንዲህ ነው:: ነገሮች ሁሉ ተበላሹ ባልንበት ወቅት ባላሰብነው ጊዜና ሰዓት እግዚአብሔር ሥራ ይጀምርና ችግራችንን ይፈታል:: አብርሃምን ከርሞ የልጅ አባት ትሆናለህ እንዳለው

እኛንም ከርሞ ይህን ታገኛለህ እንዲህ ትሆናለህ ይለናል:: ያጣነው
ጽናት ከሆነ ጽናት፣ ትዕግሥት ከሆነ ትዕግሥት፣ ዕውቀት ከሆነ ዕውቀት፣
ፍቅር ከሆነ ፍቅር ያድለናል:: ሌላም ምድራዊ ሥጋዊ ችግር ካለብን
ያንን ሰጥቶ ያስደስተናል፣ ሥራ ላጣነው ሥራ፣ ትዳር ለሌለው ትዳር፣
ቤት ለምናስብ ቤት የሚሰጥበት ጊዜ አለው:: እንደ አብርሃም እኛም
ተፈጸመ የምንልበት ጊዜ መድረሱ አይቀርም:: ለዚህ ግን ዝምታ
ያስፈልጋል:: ጊዜ ሁሉ ያንተ ነው ለእኔ የመሽ የምለው ወቅት ለአንተ
ጠዋት ነው:: እኔ ተፈጸመ የምለው ጊዜ ላንተ መነሻ መጀመሪያ ነው
ብሎ መታገሥ:: ነቢዩ በዝምታ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጉ የሚ
ለንም ለዚህ ነው::

ነቢይቱ ሐና ከነገደ አሴር የተወለደች የፋኑኤል ልጅ ነበረች::
ሉቃ.፪÷፴፮:: ይህች ሴት አሥራ አምስት ዓመት በድንግልና ከኖረች
በኋላ ባል አግብታ ሰባት ዓመት ቆየች:: ከዚያም ከባሏ ተፋታ ሰማንያ
አራት ዓመት በቤተ መቅደስ እያገለገለች ኖረች:: በአጠቃላይ መቶ
ስድስት ዓመት እስኪሆናት ከቤተ መቅደሱ ሳትርቅ ትንቢት እየተ
ናገረች በጾምና በጸሎት ተጠምዳ የጌታችንን መምጣት እየጠበቀች
ኖረች:: በመጨረሻም ጌታችን ሲወለድ ተነሥታ ለሕዝቡ ሁሉ መሰ
ከረች:: የተወለደው ሕፃን የዓለሙ መድኃኒት እንደሆነ ነገረች:: ከቤተ
መቅደስ ባለመራቋ ይህንን ሁሉ ዘመን በመታገስ የምትጠብቀውን
ሁሉ ለማየት በቃች:: ትንቢቷ ሠመረላት:: አስቀድማ የተናገረችለት
እርሱ መሆኑን አሳይታ አለፈች::

እኛም እንደ ነቢይት ሐና ነገ ይሆናል ብለን የምናስባቸው ብዙ
ጉዳዮች አሉ:: በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንዲከሰቱ የምንመኛቸው
ምኞቶች አሉ:: ለምሳሌ ሰው ሁሉ ንስሐ ቢገባ፣ ቀራቢ ቢሆን፣ ከኃጢ
አት ወደ ጽድቅ ቢመለስ ምኞታችን ይሆናል:: ሰንበት ት/ቤቶች ሁሉ
ጽናት ያለው መንፈሳዊ ወጣት ቢያፈሩ አንድ ዓይነት የዕድገት ደረጃ
ይዘው ቢራመዱ ብለን እናስብ ይሆናል:: ጉባኤያት እየሰፉ የአብነት
ት/ቤቶች ችግራቸው ተወግዶ ከአሁኑ በበለጠ ተማሪ ሲሰበሰብባቸው
ማየትም እንሻ ይሆናል:: ይህንን ያሰብነውን በዓይናችን ለማየት ግን
ትዕግሥት ሊኖረን ይገባል:: እንደ ነቢይት ሐና ነገን ለእግዚአብሔር





ሰጥቶ ወገብን ታጥቆ ማገልገል ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር አንድ
ቀን ሐሳባችንን አሳክቶ እንደሚያሳየን ምኞታችንን ፈጽሞ እንደሚ
ያስደስተን በማመን በዝምታ መጓዝ ይኖርብናል:: ነገን በተስፋ ከጠበ
ቅነው ብሩህ ሆኖ እንደሚገለጥ ማመን ይገባናል::

ጻድቁ ኢዮብ ልጆቹን ሀብቱን በአንድ ወቅት አጣ:: /መጽሐፈ
ኢዮብ ፩ እና ፪/:: እግዚአብሔርን ካድ ብላ ሚስቱ እስክትፈትነው ድረስ
ተቸገረ:: ሰውነቱም ተገልብጦ በቁስል ተመታበት:: ይህ ሁሉ ሲሆን
ግን ያጣውን እያሰበ አልተማረረም:: ይልቁን እግዚአብሔር ነገ እንደ
ሚገለጥለት የነሣውን ሰጥቶ ሊያስደስተውም እንደሚችል እያሰበ
በትዕግሥት ጠበቀ:: በዙሪያው ያለው ፈተና የሰዎች ጉትጎታ ሳይረብ
ሸው በዝምታ ቆየ:: ስለዚህም ፈጣሪው ትዕግሥቱን ተመልክቶ የወሰደበትን
ሁሉ መለሰለት:: የቀደመ ሀብቱን ጸጋውን አጎናጸፈው፤ ልጆችንም ሰጠው::

ዛሬም ቀድሞ የነበረንን ያጣን መንፈሳዊ ጥንካሬያችን ተሰርቆ ጽና
ታችን ጠፍቶ ታሪክ ተራኪ ሆነን የቀረን እንኖራለን:: ድሮ እኮ አስ
ቀድስ ነበር:: ያን ጊዜ እጸለይ ነበረ:: መንፈሳዊ ሕይወቴ እግዚአብሔ
ርን የሚያስደስት ነበረ በማለት ብቻ የምንኖር የትላንቱን ከማሰብ
ውጭ ዛሬ የምንለው የሌለን ውሉ እንደጠፋበት ቋጠሮ መንፈሳዊ ሕይ
ወታችን የተናጋብን አንጠፋም:: እንዲህ የሆንን እግዚአብሔር ወደ
ቀደመ ቦታችን እንዲመልሰን ማጉረምረም ሳይሆን መታገሥ ይገባ
ናል:: ስለማይፈልገኝ ተወኝ:: ጽናት ሳጣ መንፈሳዊ ጥንካሬ ሲለ
የኝ ዐይቶ እንዳላየ ሆነ ብለን የወሰደብንን ጸጋ እያሰብን ከማጉረምረም
ነገ የቀድሞው ሀብታችን እንደሚመለስ ተስፋ እናድ ርግ:: ሳንማረር
ፈጣሪን ደጅ እንጥና፤ አቤቱ መሬት መሆኔን አስብ የበደልኩትን
በደል ሳትመለከት ወደ ትላንትና ጽናት ወደ መጀመሪያው መንፈ
ሳዊ ሕይወት መልሰኝ እንበለው:: የኢዮብን ትዕግሥት አይቶ የወሰደ
በትን ሁሉ እንደመለሰለት እኛም ከታገሥን የተነጠቅነውን ሁሉ መል
ሰን እናገኛለን:: ነገ እንደ ትላንቱ ብሩህ ዘመን ሆኖ ይገለጥልናል::
ለሁሉም ግን በዝምታ /በትዕግሥት/ ፈጣሪን ደጅ መጥናት ያስፈልጋል::
ችግርን መከራን በጸጋ ተቀብለን እርሱን ተስፋ በማድረግ በትዕግሥት
/በዝምታ/ ለመጽናት እንድንበቃ ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን::